በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የታክስ መረጃ አያያዝንና አስተዳደርን አስመልክቶ የተከናወነ የክትትል ኦዲት /FOLLOW UP AUDIT/ ሪፖርት

የመጋቢት 2008 ዓ.ም

ማውጫ

ክፍል አንድ 3
መግቢያ 3
የባለስልጣኑ ተልዕኮ እና ራዕይ 4
የባለስልጣኑ ራዕይ 4
የባለስልጣኑ ተልዕኮ 4
የባለስልጣን መ/ቤቱ ዓላማ ስልጣን እና ተግባር 4
ዓላማ 4
የባለስልጣኑ መ/ቤት ስልጣንና ተግባር 4
የክትትል ኦዲቱ አላማ 6
የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 6
የክትትል ኦዲቱ አካባቢ 6
ክፍል ሁለት 7
በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች 7
ዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አስተዳደርን በተመለከተ፣- 7
የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር አሰጣጥን በተመለከተ 9
ግብር ከፋዮች የመክፈያ ጣቢያ ሲቀይሩ መረጃቸው የሚተላለፍ መሆኑን በተመለከተ 10
በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (በSIGTAS) እና በቅ/ፅ/ቤቶች የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ ተመሳሳይና የሚናበብ መሆኑን በተመለከተ 11
የግብር ከፋዮች የግዥ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ተጠናቅረው በመረጃ ቋት /Data Base/ በማእከል መያዛቸውን በተመለከተ 13
የታክስ መረጃ አሰባሰብና አስተዳደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መዘጋጀቱን በተመለከተ 15
በፌዴራል፣ በክልል መንግስት እና በከተማ መስተዳደሮች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ መኖሩን በተመለከተ 17
የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮችን በተመለከተ 17
የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌርን በተመለከተ 18
የሽያጭ መሳሪያዎች ጥገናን በተመለከተ 19
የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች መረጃን በተገቢው መንገድ ስለመመዝገባቸው የሚያደረግውን ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ 21
ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮች መረጃ አያያዝን በተመለከተ 22
የመረጃ አቅርቦት መስጫ ማዕከል መኖሩን በተመለከተ 23
ክፍል ሶስት 24
የክትትል ኦዲቱ (Follow up Audit) መደምደሚያዎች 24

ክፍል አራት 27
በክትትል ኦዲቱ (Follow up Audit) የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች........ 27
አባሪ 1 29
በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት ተሰጥተው የነበሩ የማሻሻያ ሀሳቦች........ 29

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በኢትዮጵያ የቀረጥና የግብር አሰባሰብ ረጅም ታሪክ ያለውና ወደ ውጭ ለሚላኩና ከሀገር ለሚወጡ መሳሪያዎች እንደየመጠናቸው በዓይነት ታክስና ቀረጥ እንዲከፈል ተደንግጎ ነበር፡፡ በመቀጠል በ1692 ዓ.ም.የቀረጥ አከፋፈል ሥርዓት ደንብ በማበጀት የቀረጥ መቅረጫ ቦታዎች፣ የቀረጡ መጠን እና ቀረጥ የማይመለከታቸውን በመለየት አፄ እያሱ አዋጅ አውጀው ነበር፡፡ ከዚያም በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በንጉስ ምስል የተሰራ ገንዘብ ሲታተም የግብርና የጉምሩክ ክፍል በ1901 ዓ.ም.ተቋቋመ፡፡ የነበረው የጉምሩክ አሠራር አንዳንድ መሻሻል እየተደረገበት እስከ ጠላት ወረራ ድረስ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ከጠላት ወረራ በኃላ ጉምሩክ በአዲስ መልክ በ1935 ተቋቋሞ ሥራውን የጀመረ ሲሆን ሥራውንም የሚያግዙ የተለያዩ አዋጆችና ደንቦች ታውጀዋል፡፡
2. ከ1966 አብዮት በኋላ በነሐሴ 1967 ዓ.ም. የጉምሩክ ቀረጥና ኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር በመባል በአዲስ መልክ ተዋቀረ፡፡ የአለም ጉምሩኮች ሕብረት ምክር ቤት ያዘጋጀውን የንግድ ሸቀጦችን በተሰሩበት ንጥረ ነገር እና በአገልግሎታቸው የሚመድበው የታሪፍ መጽሐፍ ከነሐሴ 1967 ዓ.ም.ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ፡፡
3. የጉምሩክ ቀረጥና ኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ይባል የነበረው በ1989 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 60/1989 የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በመባል ተጠሪነቱ ለገቢዎች ቦርድ እንዲሆን ተደንግጎ እንደገና ተቋቋመ፡፡ ከዚያም በአዋጅ ቁጥር 368/1995 የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለገቢዎች ሚንስቴር እንዲሆን ተደረገ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተዋህደው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን" በመባል ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደንግጎ ተቋቋመ፡፡

የባለስልጣኑ ተልዕኮ እና ራዕይ

የባለስልጣኑ ራዕይ

4. “በ2020 በአፍሪካ ግንባር ቀደም የሆነ ዘመናዊ እና ፍትሃዊ የታክስ አስተዳዳር ስርዓት ሰፍኖ አገራዊ ወጪ በአገራችን ገቢ ተሸፍኖ ማየት፡፡”

የባለስልጣኑ ተልዕኮ

5. “ታክስና ቀረጥን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር፣ ህግን ሊያስከብር የሚችል ሙያዊ ብቃትና ተነሳሽነት ያለው ባለሙያ በመጠቀም፤ ዘመናዊ የታክስ እና ቀረጥ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት፣ ለሃገር እና ለከተማ አስተዳደር ልማት የሚውል ገቢ በብቃት በመሰብሰብ የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ማረጋገጥ”

የባለስልጣን መ/ቤቱ ዓላማ ስልጣን እና ተግባር

ዓላማ

6. በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የባለሥልጣኑ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዘመናዊ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
- ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣
- ኮንትሮባንድንና የታክስ ማጭበርበርና ስወራን በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስና የጉምሩክ ሕጎችን ማስከበር፣
- ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣
- የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ናቸው፡፡

የባለስልጣኑ መ/ቤት ስልጣንና ተግባር

7. ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል ዋና ዋናዎቹ ፡-

- ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፡
- በመስኩ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስና የቀረጥ ነፃ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ለታሰበው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡

- ግብር/ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ግብር/ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የግንዘቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይተምናል፤ ተከፋይ የሚሆነውን የታክስ መጠን ይወስናል፤ ይሰበስባል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል የበለጠ አጽንኦት በመስጠትና ሌሎች ገቢዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ በጥናትና ምርምሩ ውጤት መሠረት ፖሊሲዎችንና ህጎችን ያመነጫል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
- ለገቢና ወጪ ዕቃዎች ቁጥጥርና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ በመስኩ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤ ይከሳል ይከራከራል፤ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን ዐቃቤያነ ሕግና መርማሪዎች ቡድን ያደራጃል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኙ ሠነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፤ ዘመናዊ የዕቃዎችና የሠነዶች ምርመራ አገልግሎት ላብራቶሪ ያደራጃል፤ በጥቅም ላይ ያውላል፣
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የጉምሩክና የታክስ ወንጀሎችን የመመርመር፤ የመክሰስና ኮንትሮባንድን የመቆጣጠር እንዲሁም ታክስ የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል ለክልል የፍትህ አካላትና ገቢ ሰብሳቢ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ ለአፈፃፀሙ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- ለክልል ገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣
- የታክስና የጉምሩክ አስተዳዳርን በሚመለከት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፣
- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣንና ለጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የክትትል ኦዲቱ አላማ

8. የክትትል ኦዲቱ አላማ በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተዘረጋው የታክስ መረጃ አስተዳደር ስርዓት በተመለከተ በ2006 ዓ.ም የክዋኔ ኦዲት መከናወኑ ይታወቃል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች ተግባር ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ እና ባለስልጣን መ/ቤቱ በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አድርጎ ለመ/ቤታችን የላከው የድርጊት መርሃ ግብር እየተተገበረ መሆኑን በመገምገም ችግሮች መፈታታቸውን/መሻሻላቸውን/ ለማረጋገጥ እና ባለስልጣን መ/ቤቱ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ማገዝ ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

9. የክትትል ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2006 በጀት ዓመት የባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃ አስተዳደር እና አያያዝ ስርዓት በተመለከተ የተከናወነውን የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የተገኙ ግንቶችን ለማሻሻል የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች እና ባላስልጠን መ/ቤቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ለመተግበር ያዘጋጀውን የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት አድርጎ ችግሮቱ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ የክትትል ኦዲቱ የተከናወነዉ በዋናው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ውስጥ መረጃዎችን በመከለስ፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችም ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እና አሠራሩን በአካል ተገኝቶ በመመልከት ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ አካባቢ

10. ለክትትል ኦዲቱ የተከናወነው ቀደም ሲል በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ማለትም በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነውን የታክስ መረጃ አስተዳደር ስርዓት ጊዜና ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል የተከናወነው የክዋኔ ኦዲት ወቅት የተገኙ ግኝቶች መሻሻላቸውንና ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

ክፍል ሁለት

በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች

ዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አስተዳደርን በተመለከተ፣-

11. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ግብር ከፋዮች መረጃ በጥራትና በተቀላጠፈ መልኩ በዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አስተዳደር ለመያዝ የሚያስችል የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) በእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተያዘ መረጃን የሚመዘግብና የሚቆጣጠር፣ የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥርና የጣት አሻራ መመዝገቢያ እና የጉምሩክ ቀረጥ አከፋፈልን የሚያግዝ አሲኩዳ የተባሉ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን የዘረጋ ቢሆንም በዘረጋው የመረጃ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ በአግባቡ የግብር ከፋዩን መረጃ አሰባስቦ የመያዝ የማደራጀት እና የማስተዳደር ተግባሩን በቂ ትኩረት ሰጥቶት ተግባራዊ አድርጎት አልተገኘም፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በአጠናው የመሰረታዊ የአሰራር ስርዓት ለውጥ ጥናት የሁሉም ግብር ከፋይ ሀብት እና ንብረት ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት እንደዘረጋ ቢገለፅም በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ የሁሉንም ግብር ከፋዮች ሀብትና ንብረት መዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በባለስልጣን መ/ቤቱ የተደራጁት የመረጃ ቋቶች እርስ በርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ ተደርገው ያልተሰሩ መሆኑን፣ የተሰበሰበዉ መረጃ ተደራጅቶ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት የጥራት ደረጃውን ለመገምገምና ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ በተበታተኑ የመረጃ ቋቶች የተያዘው መረጃም ሆነ ከሶስተኛ ወገን በተለያየ ዘዴ የተሰበሰበው መረጃን የመሰብሰብና ተንትኖ የማጠናቀር እንዲሁም የማሰራጨት ተግባር ከዋናው መ/ቤት በስተቀር በቅ/ፅ/ቤቶችና በክልሎች እንደማይከናውን ታውቋል፡፡ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ክልሎች መረጃዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረገው ጥያቄ ሲቀርብ ብቻ መሆኑና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረጉ መረጃዎችም ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ግብረ መልስ የማይሰብሰብ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

12. በክትትል ኦዲቱ እንደታየው ባለስልጣን መ/ቤቱ የግብር/ታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ለማሻሻል የተለያዩ የመረጃ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም እና በማስተዳደር ትርጉም ያለው ስራ እየሰራ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ቴክኖሎጂዎች የሚፈለገውን ያህል አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ እና የተዘረጋውም የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓቶች የማይመጋገቡ መሆናቸው ታውቋል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት መበልፀግ ያለባቸው ሲስተሞች በሚመለከተው ክፍል ተለይተው የተጠየቁ ቢሆንም ከሁለት አመት በላይ ችግሮቹ ያልተፈቱና መልስ ያልተሰጠባቸው መሆኑን ከቀረቡ ማስረጃዎችና ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን አቅም ለማሳደግ በሚመለከተው ክፍል ተጠይቀው እስካሁን መልስ ያልተሰጣቸው እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

- የሽያጭ መረጃን የማስገቢያ ሲስተም፣
- የግብር ከፋዮችን የሀብት መረጃ/ የቤት፣ መኪና እና የአክሲዮን ድርሻ/ ማስገቢያ ሲስተም ፣
- የህትመት መረጃ /ለንግድ ሥራ የሚታተሙ መፅሄቶችና ጋዜጦች/ ማስገቢያ ሲስተም፣
- የመረጃ ማጠናቀሪያና መተንተኛ ሶፍትዌር /ማጠቃለያ ሪፖርት/ ሲስተም፣
- ከግብር አወሳሰን ግብረ-መልስ መያዥያ ስስተም፣
- የወጪ መጋራት መረጃ ኦን ላይን መመዝገብ የሚያስችል ሲስተም፣
- የ ECX መረጃን ኦን ላይን መመዝገብ የሚያስችል ሲስተም የሚሉ ናቸው፡፡

13. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ግብር ከፋዮች መረጃ በጥራትና በተቀላጠፈ መልኩ በዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አስተዳደር ለመያዝ የሚያስችል የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን እየተጠቀመ የሚገኝ ቢሆንም በተለያየ ጊዜ ችግሮች የሚያጋጥሙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በቴሌ ምክንያት (ጂ.ፒ.አር.ኤስ) በማይደርስበት ቦታ ቴክኖሎጂውን መጠቀም አለመቻል፣ የግብር ከፋዮች መረጃዎች የማይመጋገቡ መሆኑ ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማቆየት አለመቻሉ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት ከቴሌ ጋር ያለው ችግር እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን ሌሎቹንም ችግሮችን ለመቅረፍ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

14.እንዲሁም የመረጃ ቋቶች እርስ በርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ (Interface & Intranet) ተደርገው ያልተሰሩ መሆኑ እና መረጃዎችም ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ግብረ መልስ በማንዋል የሚሰበሰብ ቢሆንም በሲስተም የተደገፈ ባለመሆኑ በቀላሉ ጥቅም ላይ ለማዋል አልተቻለም፡፡ይህን በተመለከተ የሚመለከታቸው ኃላፊ ለክትትል ኦዲት ቡድኑ በሰጡት መልስ በአሁኑ ሰዓት እየተገለገሉበት ያለው ኢንተርፌስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ብቻ የሚያቀባብል በመሆኑ የሚፈለጉትን መረጃዎች ሁሉም የሚናበቡ አለመሆኑ፤ ምክንያቱም የተዘረጉት ሲስተሞች በተናጥል ስለሆነ ውስን አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ሲሆን መረጃዎችን ለማደራጀት፣ ለማጠናቀርና ለመተንተን የቴክኖሎጂ አቅምን ለመገንባት ጥናት ተደርጎ ለሚመለከተው ኃላፊ ቀርቦ በሂደት ላይ ያለ መሆኑ እንዲሁም መረጃዎች የሚጠናቀሩት በስጋት ደረጃ (Risk based) ለተመረጡት እንጂ የሁሉም ግብር ከፋዮች አለመሆኑ፤ ቅ/ጽ/ቤት የግብር ከፋዮችን መረጃ ለማጠናቀር ስራዎች የተጀመሩ መሆኑን እና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ክልሎች መረጃዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረገው ጥያቄ ሲቀርብ እና በየ3ወሩ ሳይጠየቅ የሚሰራጭ ሲሆን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረጉ መረጃዎችም ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ግብረ መልስ በማንዋል የሚሰበሰቡ መሆኑንገልፀዋል፡፡

15. እንዲሁም የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን አቅም ለማጎልበትና የሚፈለገውን ያህል አገልግሎት ለመስጠት በአገር ውስጥ ታክስ በስራ ላያ ያለውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ችግሮችን በመለየት በድርጊት መርሃ ግብር ታክስ በኢንተርኔት ከማስታወቅ (SIGTAS-E-Tax) የግዥና መረጃን ከማስታወቅ (E-Filing) ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች ለመቅረፍ በ መጋቢት 2007 ዓ.ም ለሚመለከተው አካል ያቀረብን ቢሆንም በሂደት ላይ ያለ በመሆኑ እስካሁን ችግሮቹ ሊፈቱ አለመቻላቸውን ገልፀዋ፡፡

16. የተዘረጋው የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊነት በየጊዜው እንዲዳብርና እንዲበለፅግ ባለመደረጉ የግብር ከፋዩ ለእንግልትና ለወጪ ይዳርጋል፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት ጥራት ይቀንሳል፣ የግብርና ታክስ አሰባሰቡ እንዳይጨምርና የሰራተኞችን ውጤታማነት እንዲቀንስ ከማድረጉ በላይ መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት ላይ አሉታዩ ተፅዕኖ የሚያሳርፉ ይሆናሉ፡፡

የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር አሰጣጥን በተመለከተ

17. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ ስርዓት አፈፃፀም መመሪያ 11/2001

አውጥቷል፡፡ በመመሪያውም ላይ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ መለያ ቁጥር ሊሰጠው እንደማይችል ያስቀምጠ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡት ቅ/ፅ/ቤቶች 26 የሚሆኑ ግብር ከፋይዎች በሁለት መለያ ቁጥር (TIN) ተመዘግበው ተገኝተዋል፡፡

18. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከቀረበው ቃለ መጠይቅ እንደተረዳነው የግብር ከፍይ መለያ ቁጥር አጀማመር ላይ የነበሩ ችግሮች ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት ከአንድ በላይ የመለያ ቁጥር የማይሰጥ መሆኑ፣ ቀደም ብሎ የተከሰተውም በ"Fictitious TIN" ምክንያት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ስራ ላይ ከዋለው 10 ዲጂት ቲን ቁጥር ያነሰ ስለሆነ በምንም መልኩ ስራ ላይ ሊውል የሚችልበት መንገድ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የተቋሙ መረጃ ዳይሬክቶሬት ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸው በመረጃ ቴክኖሎጂ የማጥራት ስራ የሚከናወን መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በተገኙት ግኝቶች የማጥራት ስራ ተሰርቶ ምን ያህሉ በክትትል ተገኝተው መታረማቸው እና በአሁኑ ወቅት ከአንድ በላይ የመለያ ቁጥር የያዘ ግብር ከፋይ የሌለ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ወይም ማስረጃ መስጠት አልቻሉም፡፡

19. በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተጠቀሰውም ሆነ በሌላ ምክንያት የመረጃዎች ልዩነትና ሰህተቶች ሲኖሩ በጊዜው መከታተልና ማረም ካልተቻለ ስህተቶች በመጠራቀም ለማረም የሚያስቸግሩ ከመሆናቸው በላይ በመረጃዎች ላይ የሚኖረውን ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ ሊከት ይችላል፡፡

ግብር ከፋዮች የመክፈያ ጣቢያ ሲቀይሩ መረጃቸው የሚተላለፍ መሆኑን በተመለከተ

20. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት
    - 62 ግብር ከፋዮች በተቋሙ ስር ከሚገኙት 10 የታክስ ማዕከሎች ውጭ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 25 ግብር ከፋዮች "አዲስ አበባ ቫት" በሚባል የተመዘገቡ ሲሆን፣ 37 ግብር ከፋዮች "አዲስ አበባ ገቢዎች ባለስልጣን" በተባለ በተዘጋ ታክስ ማእከል የተመዘገቡ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅ/ጽቤት (ታክስ ማዕከሎች) በሚቀይሩበት ወቅት ፋይላቸው ከነሙሉ መረጃቸው መዘዋወር አለመዘዋወሩን ለመከታተል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋ እና ለዝውውር ሂደቱ የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)ን አለመጠቀማቸው በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡

21. በክትትል ኦዲቱ እንደታየው ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ሲቀይሩ በSIGTAS ያለው መረጃ ወደቀየሩበት ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ወዲያው የሚዛወር ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ማህደራቸው ግን አብሮ የማይዛወር መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

22. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አንድ የግብር ከፋይ ቅ/ጽ/ቤት ሲቀይሩ ወዲያውኑ በSIGTAS ያለው መረጃ ወደ ቀየሩበት ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ የሚዛወር ሲሆን የማህደር ርክክብ በቃለ ጉባኤ በመያዝ የሚረካከቡ መሆኑን ይህ ካልሆነ ግብር ከፋዩ መስተናገድ የማይችልበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ቢሉም ቀደም ብሎ ስለተገለፁት 62 ግብር ከፋዮች በተቋሙ ስር ከሚገኙት 10 የታክስ ማዕከሎች ውጭ ማለትም 25 ግብር ከፋዮች "አዲስ አበባ ቫት" 37 ግብር ከፋዮች "አዲስ አበባ ገቢዎች ባለስልጣን" በተባለ በተዘጋ ታክስ ማእከል ተመዝግበው ስለነበሩት በአሁኑ ወቅት ችግሩ ስለመቀረፉ የሰጡት ምላሽም ሆነ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት እነዚህ ግብር ከፋዮች ባስመዘገቡበት አድራሻ በተጨባጭ የሚሠሩበት ሥራ ተፈትሾ በማረጋገጥ የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት ዕቅድና የድርጊት-መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ የሚተገበርበት አቅጣጫ እየታየ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም ይህን ስለመተግበራቸው የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

23. ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ጣቢያ ሲቀየሩ መረጃቸው ሙሉ በሙሉ መዘዋወሩ የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በግብር ከፋዩ ላይ እንግልት፣ ለአላስፈላጊ የጊዜና የወጪ ብክነት በመዳረግ ና በየጊዜው መረጃዎችን በማጥራት የሚሰጠውን አገልግሎት የተቀላጠፈ እንዳይሆን በማድረግ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈጠሩና እንዲጎሉ ያደርጋል፡፡

በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (በSIGTAS) እና በቅ/ፅ/ቤቶች የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ ተመሳሳይና የሚናበብ መሆኑን በተመለከተ

24. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኙት
    - በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት አምስት የታክስ ማዕከላት በግብር ከፋይነት ተመዝግበው የተያዙት 21,595 ግብር ከፋዮች ሲሆኑ፣ በማዕከል በተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) በአምስቱ ቅርንጫፎች ያሉ ተብሎ ተመዘገቦ የተያዘው 29,792 ግብር ከፋዮች መሆናቸው፣ ይህም በማእከል በSIGTAS ተመዝግቦ የተያዘው በ8,197 በብልጫ የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል ፡፡

- ከላይ ከተጠቀሱት ግብር ከፋዮች ውስጥ በአምስቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በስራ ላይ ያሉ (Active) ተብለው የተያዙ 20,047 ግብር ከፋዮች ሲሆኑ በSIGTAS ላይ በሥራ ላይ ያሉ ግብራቸውን የሚያሳውቁ (active) ተብለው የተያዙት 28,287 ግብር ከፋዮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም በ(active) በግብር ከፋይነት በSIGTAS ላይ የተመዘገቡት ግብር ከፋዮች በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ከያተዙት በ8,240 ግብር ከፋይ በብልጫ በልዩነት ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በግብር ከፋይነት የተመዘገቡ 37 ግብር ከፋዮች በSIGTAS ላይ ምዝገባቸው በሌላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት (የታክስ ማዕከል) ላይ ተመዝግበው የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በመዝገብ ቤት በማህደር ተይዘው የሚገኙ መረጃዎችን የማጥራት ተግባር እንዳልተከናወነ እና በSIGTAS ተመዝገበው የተያዙ የግብር ከፋይ መረጃዎች በየጊዜው እየተገመገመ ወቅታዊ የማይደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና በተሸሻለው አዋጅ ቁጥር 608/2001 መሰረት ግብር ከፋዩ የሚያደረጋቸውን ማንኛውም ለውጦች በግብር ከፋይነት በተመዘገበቡበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እየቀረበ ማሳወቅ እንደሚገባው እና በየጊዜው የማያሳውቁ ግብር ከፋዮች ተጠያቂ ሊደረጉ እንደሚገባ የተገለጸ ቢሆንም ይህ ተግባራዊ ተደርጎ አልተገኘም፡፡

25. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ችግሮቹ ሊፈጠሩ የሚችሉት በማህደር ከተዘጉ በውኃላ በሲስተም ላይ የተዘጋበት ቀን ሳይሞላ ከቀረ የሚፈጠር መሆኑን ገልፀው በየወቅቱ የመናበብ እና ግብረመልስ የመስጠት ችግር ምክንያት የሚከሰቱ ሲሆን ችግሮቹን ለመፍታት እየሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ከላይ የተገለፁት የቁጥር ብልጫዎች በአሁኑ ወቅት ስለመስተካከላቸው ወይም መረጃዎችን የማጥራት ስራዎች ስለመስራታቸው ማስረጃ አላቀረቡም፡፡

26. በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተጠቀሰውም ሆነ በሌላ ምክንያት የመረጃዎች ልዩነትና ሰህተቶች ሲኖሩ በጊዜው መከታተልና የማረም ኃላፊነታቸውን እየተወጡ አለመሆኑ እና በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኙ ግኝቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድ አለመቻሉ ከክዋኔ ኦዲቱ ሊጨምርላቸው የሚችለውን ዋጋ ጥቅም እላይ እንዳይውል ያደርገዋል፡፡

የግብር ከፋዮች የግዥ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ተጠናቅረው በመረጃ ቋት /Data Base/ በማእከል መያዛቸውን በተመለከተ

27. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው

- የሁሉም ግብር ከፋዮች የግዢ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች እና የ3ኛ ወገን መረጃዎች በተሟላ መልኩ የማይሰበሰቡና የተሰበሰቡትም መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ በማዕከል ደረጃ ወደአለው የመረጃ ቋት ተጠቃሎ አለመግባቱን፣ በተለይም የ2003 እና የ2004 በጀት ዓመታት የግዢ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ግን ሙሉ በሙሉ ወደ መረጃ ቋት አለመግባታቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የግብር ከፋዮች መረጃ ለውሳኔም ሆነ ለሌሎች ተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ እንደ የሥራ መስኩ እና ዓይነት እየተለዩ (ለምሳሌ በግብርና ዘርፍ፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፎች ወዘተ) ተደራጅተው እንዳልተያዙ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ውዝፍ ዕዳ ያለባቸውን ግብር ከፋዮች፣ ግብር ከፋዮች የሚያቀረቡትን የቅሬታና አቤቱታ የሚመለከቱ መረጃዎች፣ የተሰጡ ውሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃችን የሚገልጹ መረጃዎች በተደራጀ ሁኔታ ተጠናቅረው አለመያዛቸው ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃው በሚመዘገብበት ወቅት ግብር ከፋይ ማቅረብ የሚገባቸው ዋና ዋና መረጃዎች እንደ የባንክ አካውንት፣ የተሰማሩበት የስራ ዘርፍ፣ የግብር እፎይታ ጊዜ ተጠቃሚ ከሆኑ ደግሞ ዕፎይታው የሚያልቅበት ጊዜ እንዲሁም ወቅታዊ አድራሻዎች በተሟላ ሁኔታ በSIGTAS አለመመዝገቡን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የግብር እፎይታ ጊዜ (Tax holiday) ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የዕፎይታ ጊዜያቸው መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚያበቃና ያሉበትን ደረጃ የሚገልጽ መረጃና ሌሎች መረጃዎች በተሟላ መልኩ ተደራጅተው አለመያዛቸውን ባለሥልጣኑ ያቋቋመው አገር ውስጥ ታክስ የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ቡድኑ ሪፖርት ላይም ተገልጿል፡፡

28. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው መረጃዎቹ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ከክልሎች ጋር በደብዳቤ እና በሀርድ ኮፒ የሚደረግ ልውውጥ መሰረት መረጃዎች ወደ መረጃ ማዕከል የሚገባ ቢሆንም ወቅታዊ (up to date) አለመሆኑ እና ከዋናው መ/ቤት የተጠናከረ መረጃ በየ3ወር ለሚመለከታቸው ለቅ/ጽ/ቤቶች የሚላክ ቢሆንም ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው የተቀመጡ እና እየተሰበሰቡ ያሉ የሽያጭ መረጃዎች ለግብር አወሳሰን በተሟላ እና በጠራ መልኩ እንዲጠቀሙ ማድረግ አለመቻሉ ና በሚፈለገው

ያክል በመረጃ መደገፍ አለመቻሉ እንዲሁም ይህን ችግር የሚቀርፍ የመረጃ ቴክኖሎጂ አቅም ያልተገነባ መሆኑ ታውቋል፡፡

29. በክትትል ኦዲቱ በ2007 በጀት ዓመት የቀረቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ትንተና መሰራቱ የሚበረታታና ግልፅ የሆነ አሰራር እንዲሰፍን የሚያግዝ መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ከተገልጋዩ የቀረበው የቅሬታ አቤቱታ 58% የሚሆነው የህግ አግባብነት ያለውና ለባለጉዳዩ የተወሰነ በመሆኑ በቅ/ጽ/ቤቶች የቅሬታ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት ትንተና ሪፖርት ላይ ለበላይ አመራሩ ቀርበው የነበሩና በአሰራር መመለስ ያለባቸው ችግሮች ላይ የአሰራር ለውጥ ባለመደረጉ ችግሮቹ በቀጣዩም አመት እንደችግር እንደተጠቀሱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. በተጨማሪም መረጃው በሚመዘገብበት ወቅት ግብር ከፋይ ማቅረብ የሚገባቸው ዋና ዋና መረጃዎች እንደ የባንክ አካውንት፣ የተሰማሩበት የስራ ዘርፍ፣ የግብር እፎይታ ጊዜ ተጠቃሚ ከሆኑ ደግሞ እፎይታው የሚያልቅበት ጊዜ እንዲሁም ወቅታዊ አድራሻዎች በተሟላ ሁኔታ በSIGTAS የሚመዘገብ ስለመሆኑ እና የግብር እፎይታ ጊዜ (Tax holiday) ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የእፎይታ ጊዜያቸው መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚያበቃና ያሉበትን ደረጃ የሚገልጽ መረጃና ሌሎች መረጃዎች በተሟላ መልኩ ተደራጅተው ስለመያዛቸው ለክትትል ኦዲት ቡድኑ መረጃው አልቀረበም፡፡በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶችን እንደግብዓት በመጠቀም ችግሮችን ለመፍታት የተደረገው እንቅስቃሴ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

31. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ግብር ከፋዮች የግዢ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች እና የ3ኛ ወገን መረጃዎች በማዕከል ደረጃ ወደአለው የመረጃ ቋት የሚገባበት ስርዓት መኖሩ እንዲሁም መረጃዎች ተሰብስበውና ተጠናቅረው በየሶስት ወሩ ለተጠቃሚው ቅ/ጽ/ቤት በመላክ ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆኑን ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ወቅታዊ አለመሆኑ (በክትትል ኦዲቱ ሰዓት የዘጠኝ ወር ያልተጠናቀረ መረጃ መኖሩን) ፤የተሰበሰበ መረጃ ከተመዘገበ በውሃላ 10% ናሙና በመውሰድ ጥራቱን የማረጋገጥ ስራ እንደሚሰራ፤ እንዲሁም የ2003 እና የ2004 በጀት ዓመታት የግዢ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ግን ሙሉ በሙሉ ወደ መረጃ ቋት መግባቱን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የግብር ከፋዮች መረጃ በየሥራ መስኩ እና ዓይነት እየተለዩ (ለምሳሌ በግብርና ዘርፍ፤ በኮንስትራክሽን ዘርፍ፤ በኢንዱስትሪ ዘርፎች ወዘተ-)

ተደራጅተው የሚያዙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በየሥራ መስኩ (በዘርፍ) ተደራጅተው ስለመቀመጣቸው ማስረጃው አልቀረበም፡፡

32. ይህ በመሆኑ ከግብር ከፋዮ የሚቀርበው ቅሬታን ለመቅረፍ ተገቢ ትኩረት አለመስጠቱን፣ በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ ተደርገው ያልተገኙና ግኝቶቹም ያልተቀረፉ መሆናቸው እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግና ተገቢ ትኩረት በመስጠት የግብር ከፋዩ ግብር የመክፈል ኃላፊነቱን በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዳይወጣና በአገልግሎቱ እንዳይረካ በማድረግ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲባባሱ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

የታክስ መረጃ አሰባሰብና አስተዳደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መዘጋጀቱን በተመለከተ

33. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት

- በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃዎችን በአይነታቸው እየለየ ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀት እና ተንተኖ በማሰራጨት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲና ስትራቴጂ ያላዘጋጀ መሆኑ፤
- እንዲሁም አገር አቀፍ የግብር መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀት እና አስተዳደርን ወጥ እና ተመጋጋቢነት ያለው ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

34.በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከ 2004 ዓ.ም ጀምሮ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አሰረጫጨት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ቀርጾ ያሰራጨ ቢሆንም በአገር አቀፍ ደረጃ የግብር መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀት እና አስተዳደርን ወጥ እና ተመጋጋቢነት ያለው ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ ምክንያት በአገሪቱ ባሉ የግብር ማዕከላት የመረጃ አሰባሰብ ወጥነት የሌለው መሆኑ ታውቋል፡

35.በተጨማሪም የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና ትንተና በፌዴራል ከፍተኛና መካከለኛ ጽ/ቤቶች የታክስ መረጃ አስተዳደር በስራ ሂደት ደረጃ የተደራጀ ቢሆንም ይህ አደረጃጀት ለአዲስ አበባ አስተዳደር መካከለኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤቶች የሌለ በመሆኑ የታክስ መረጃ አያያዝ በዋና መ/ቤት እንዲሰራ መደረጉ ይህም በመረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት፣ ትንተናና ስርጭት እና በአገልግሎት አሰጣጥ ሆነ በክትትል ረገድ ወጥ

የሆነ፤ ተደራሽና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዳይሰጥ እንቅፋት መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

36.የታክስ መረጃ አስተዳደር አደረጃጀት በሌላቸው ቅ/ጽ/ቤቶችመረጃ መረጃዎች ተሰብስቦ ለዋናው መ/ቤት ለታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሚላክ በመሆኑ የሚከተሉት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

- ግብር ከፋዩ የተለያዩ መረጃዎችን በሚፈልግበት ወቅት ዋና መ/ቤት ድረስ ለመሄድ የሚገደድበት ሁኔታ መኖሩ፣
- በግብር ከፋዩ የታክስ መረጃዎች ላይ ማሻሻያም ሆነ የሚታከል መረጃ ሲኖር አሊያም የተፈጠሩ ስህተቶችን ለማረም ግብር ከፋዩ ወደ ዋና መ/ቤት የሚጠራበት ሁኔታ መኖሩና ሲጠሩም አብዛኞቹ የማይመጡ በመሆኑ ለጊዜና ለሀብት ብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ የጠራ መረጃ ለማግኘት አለማስቻሉ፤
- ስራው በዋናው መ/ቤት እንዲሰራ መደረጉ የሚፈለገው መረጃ ከሁሉም ግብር ከፋዮች ለመሰብሰብ አለማስቻሉ እና ግብር ከፋዩን በቅርበት አግኝቶ የተፈጠሩ ስህተቶችን ማረም አለመቻሉ፣
- ወደ ኮምፒውተር ሲስተም ከማስገባት ውጪ የሚጨምር እሴት አለመኖሩ፣
- የተሟላ መረጃ እንዳይኖር የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣
- የመረጃው ቀሪ ሰነድ በዋናው መ/ቤት እየተከማቸ የመጣና ቦታ የጠየቀ መሆኑ ፣
- በመረጃ መጓደል ምክንያት የተሻለ ግብር/ታክስ መሰብሰብ ያላስቻለ መሆኑ የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

37. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የተገለፁት ችግሮች የተለዩ ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ የቀረቡ ሲሆን አደረጃጀቱ ይፈታቸዋል ተብለው የሚጠበቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

38. የታክስ መረጃን መረጃው ከሚመነጭበት አካባቢ ሰብስቦና አደራጅቶ አስተዳድሮ ባለመያዙ መረጃ አሰባሰቡ፣ አመዘጋገቡና አደረጃጀቱ ምቹና ወጪ ቆጣቢ እንዳይሆን ማድረጉ፣ስራዎች ተጀምረው በሚያልቁበትና ውጤት በሚሰጡበት ቦታ ማጀራጀት የሚለውን መርህ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣ ዋናው መ/ቤት እሴት የሚጨምሩ ስራዎችን እንዳይሰራ ጊዜና ሀብት ከማባከኑም በላይ አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ተደራሽ በማድረግ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መቅረፍ እንዳይችልና በትክክለኛ

መረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ የመስጠት አቅም በማጎልበት ዜጎችን የማገልገል ተልዕኮውን በአግባቡ እንዳይወጣ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

በፌዴራል፣ በክልል መንግስት እና በከተማ መስተዳደሮች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ መኖሩን በተመለከተ

39. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው

- በኦዲቱ ወቅት በክልሎች እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ለመፈራረም በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

40. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው ባለሥልጣን መ/ቤቱ በክልሎችና በባለሥልጣን መ/ቤቱ መካከል የማግባቢያ ሰነድ አዘጋጅቶ አወያይቶ ያፀደቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮችን በተመለከተ

41. በክዋኔ ኦዲቱ እንደታየው በደንቡመሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን መጠቀም ያለባቸው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዮት በከፍተኛ ግብር ከፋዮች በባህርዳር፣በሀዋሳ፣ በምዕራብና በምስራቅ አ/አ ቅ/ጽ/ቤቶች በSIGTAS ተመዝግበው ከተያዙት 29,792 ግብር ከፋዮች ውስጥ 12,090 ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚ ሲሆኑ 17,702 (59.41%) ግብር ከፋዮች ተጠቃሚ ያለመሆናቸው ታውቋል፡፡

42. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው የሽያጭ መሳሪያ አጠቃቀምና ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት አፈፃፀም መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ የተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም በክልል ያሉት የፌዴራል ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ማስገባት ሲገባቸው ያላስገቡ መረጃ በማጠናቀርና በመተንተን ለአስተዳደራዊ ቅጣት የሚያመች በሰነድ መዘጋጀቱ ታውቋል ፡፡

43. እንዲሁም የሽያጭ መሳሪያ መጠቀም ያለባቸው የደረጃ ሀ ግብር ከፋዮች እስከ ሰኔ 30/2007 ድረስ 127,801 ደረጃ ለ ግብር ከፋዮች 113,338 በድምሩ 241,139 ሲሆኑ ከነዚህ ግብር ከፋዮች ውስጥ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም ላይ ያሉ 125,506 በመቶኛ 52% የነበረ ሲሆን በ2008 በጀት አመት በ6ወር የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንደተገለፀው በፌዴራል ቅ/ጽ/ቤት መግዛት ከነበረባቸ 20,402 ግብር ከፋዮች

የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የገዙት 17,758 87% በመቶ እና በደቡብ አዋሳ እና በአማራ ባህርዳርን ጨምሮ 38,967 መግዛት ሲኖርባቸው 29,156 (75%) የገዙ መሆኑ ታይቷል፡፡

44. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሽያጭ መሳሪያ አጠቃቀም እየተሻሻለ መምጣቱን ገልፀው መጠቀም የሚገባቸው ግብር ከፋዩች ሁሉንም ወደ ስርዓት ለማስገባትና እርምጃ ለመውሰድ ክትትል እያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

45. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መሳሪያ አጠቃቀምን ለማሻሻል እያደረገ ያለው ክትትል ተገቢና አፈፃፀሙ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ይህ ስራ ቀጣይነት ያለው በተደጋጋሚ የሚከሰት በመሆኑ አሁንም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌርን በተመለከተ

46. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- ባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ባልሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሶፍትዌር መጠቀም በህግ እንደሚያስጠይቅ በተሻሻለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 47 ቁጥር 1 ላይ የተገለፀ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩ በከፍተኛ ግብር ከፋይነት የተመዘገቡ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ 14 ሆቴሎች ባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ባልሰጠው ሶፍትዌር እየተጠቀሙ መሆኑን እና ባለስልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መረጃቸውን በአግባቡ ማስገባታቸውንና መረጃው ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የመረጃ ቋት ጋር የተገናኘ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ እና በህጉ መሠረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- ከዚህም በተጨማሪ በሂልተን እና በሸራተን አዲስ ሆቴሎች ከአገልግሎት ውጭ የተደረጉ 22 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመመሪያው መሰረት በአስመጪዎቹ ዘንድ መቀመጥ ሲገባው በሆቴሎቹ መጋዘኖች ውስጥ ለረዥም ጊዜ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

47. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሶፍትዌር አጠቃቀም ቀደም ሲል የተዘጋጀው የሶፍትዌር የመፈተሻ መስፈርቱ stand alone software ስለነበር ይህ ደግሞ ለትላልቅ ሆቴሎች አለማቀፋዊ አሰራር ለመጠቀም የማያስችል

በመሆኑ በደንብ ቁጥር 139/99 አ-3 መሰረት ተጠቃሚነት ግዴታ ለማስፈፀም (server based) ሰርቨሮችን መሰረት ያደረገ የፍተሸ መስፈርት ለማካሄድ ከአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ፋኩልቲ ጋር በመሆን ወደ ስርዓት እንዲገቡ በማድረግ በአሁኑ ሰዓት ሁሉም ሆቴሎች በባለስልጣኑ እውቅና ባገኙ መሳሪያዎችና ሶፍትዌሮች እንዲጠቀሙ ተደርገዋል፡፡ ከባለስልጣኑ ዕውቅና ውጭ ሶፍትዌር የሚጠቀሙ ድርጅቶችን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለህግ የሚያቀርቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

48. ከአገልግሎት ውጭ ስለተደረጉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በሰጡት መልስ የተገለፁት ሆቴሎች በርካታ ማሽኖች በአንድ ጊዜ የሚጠቀሙ በመሆኑ እና መጠባበቂያ /ተለዋጭ/ ማሽን ያላቸው እና ብልሽት ሲያጋጥማቸው ለመተካት የሚገለገሉበት መሆኑ በተጨማሪም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የታዩት ማሽኖች ወደ አገልግሎት ማዕከል ተመለሱ መሆኑ እና ይህ በየጊዜው ሊከሰት የሚችል አሰራር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የሽያጭ መሳሪያዎች ጥገናን በተመለከተ

49. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የታየው

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችም ሆነ አቅራቢዎቹ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 133/1999 መሰረት መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ሆኖም ግብር ከፋዩ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎች ገዝቶ ከሚጠቀምባቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በአማካይ በዓመት 15,670 የሚሆኑት በብልሽት ምክንይት ለጥገና የሚገቡ ሲሆን 7,146 (46%) በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሲወጡ የቀሩት 8,320 (54%) በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው እንደማይወጡ፣ አገልግሎት ላይ ከዋሉ ከአንድ አመት በላይ የሆናቸው 72,964 የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች አመታዊ ምርምራ በተሟላ መልኩ እንደማይደረግላቸው እና ባለሥልጣን መ/ቤቱም በህጉ እና በገቡት ግዴታ መሰረት ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎችን በመከታተልና በመቆጣጠር እርምጃ የማይወስድ መሆኑ ታውቋል፡፡

50. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ኦፕሬሽን ቡድን የ2007 በጀት ዓመት ሪፖርት ሰኔ 2007 የአዲስ አበባ ባቀረበው መሠረት ለጥገና የገቡ መሣሪያዎች ብዛት 19,671 በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው የወጡ 15,921 (81%) እና

በ2007 ዓመታዊ የዕድሳት ምርመራ የተደረገላቸው 49,170 ውስጥ በ48 ሰዓት ተጠግነው ሥራ እንዲቀጥሉ የተደረጉት ብዛት 47,286 (96%) መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

51. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በ48 ሰዓት እንዲጠገኑ ከአቅራቢዎች ጋር ወርሃዊ ምክክር በመጀመር በአቅራቢዎች በኩል ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ድጋፍ እና ክትትል እያደረጉ መሆኑን ከዚህ ውስጥም መለዋወጫዎች ከቀረጥ ነፃ ማስገባት እንዲችሉ እና የውጭ ምንዛሬ ችግር እንዲፈታ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር እና ለብሔራዊ ባንክ ደብዳቤ በማሳወቅ ድጋፍ ተደርጓል ብለዋል፡፡

52. እንዲሁም ባለስልጣኑ የሽ/መ/መሳሪያ አቅራቢዎች እውቅና ከሰጣቸው በውሃላ ለግብር ከፋዮች እያቀረቡ መሆናቸውን በቂ ክትትል እያደረጉ መሆኑን ህግን ተላልፎ ለተገኙ አቅራቢዎችም ሆነ ቴክኒሻኖች ጥብቅ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን ከቀረቡ ማስረጃዎችና ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

53. በመሆኑም መሳሪያዎች ሲበላሹ በአፋጣኝ ተጠግነው ስራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ የአቅራቢዎችን ችግሮች ለመፍታት ድጋፍ እንዲሁም በአግባቡ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ክትትል ማድረግ ተገቢ መሆኑ በኦዲት ቡድኑ ታምኗል፡፡

የንግድ ፍቃድ የሚመልሱ ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚቋረጥበት ስርዓትን በተመለከተ

54. በክዋኔ ኦዲቱ እንደታየው የንግድ ፈቃድ የሚመልሱ የግብር ከፋዮች ይጠቀሙበት የነበረው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አገልግሎት ከመስጠት የሚቋረጥበት እና በምን መልኩ መረጃው ወጥቶ መያዝ እንዳለበት የሚያሳይ ሥርዓት ያልተዘረጋና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

55. በክትትል ኦዲቱ ወቅት የታየውን ችግር ለመፍታት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አወጋገድ እና አስተዳደር ስርዓትን ለመወሰን ረቂቅ ጥናት በሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ገቢ ሰብሳቢ አመራሮች ግብዓት ተሰጥቶበት የመጨረሻ ቅርፅ ይዞ ያለበት ሁኔታ መኖሩ ና መመሪያው ተግባራዊ ሲደረግ የተጠቀሱትን ችግሮች እንደሚፈታ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

56. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አወጋገድ እና አስተዳደር ስርዓትን ለመወሰን ረቂቅ ጥናት ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ባለመጀመሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት እንቅፋት ይሆናል፡፡

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች መረጃን በተገቢው መንገድ ስለመመዝገባቸው የሚያደረግውን ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ

57. በክዋኔ ኦዲቱ እንደታየው

- በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተመዘገቡ የሽያጭ መረጃዎች ወደ መረጃ ቋት መተላለፍ አለመተላለፋቸው በየታክስ ማዕከሉም ሆነ በዋናው መ/ቤት ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚቻልበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ የሽያጭ መመዘግቢያ መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ መዋል ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2005 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ለግብር ከፋዩ ከተሸጡት 82,141 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ውስጥ 72,964 (89%) አገልግሎት ላይ የዋሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 8,755 (12%) ብቻ የሽያጭ መረጃን ወደ መረጃ ቋት የሚያስተላልፉ ሲሆኑ፣ የተቀሩት 64,209 (88%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሽያጭ መረጃን ወደ መረጃ ቋት የማያስተላልፉ መሆኑን፣ እና 5,888 (12%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ከሲስተሙ ጋር ያልተያያዙ መሆናቸው በኦዲቱ ወቅቱ ታውቋል፡፡
- የአማራ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በሥራቸው ያሉ ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ክትትል የሚያደርጉ ቢሆንም መሳሪያዎቹ መረጃዎችን ወደ ዋናው ዳታ ቤዝ ማስተላለፍ አለማስተላለፋቸውን ግን ለማረጋገጥ በዋናው ዳታ ቤዝ የሚያዘውን መረጃ ለማየት ፓስ ወርድ ስላልተሰጣቸው ማረጋገጥ እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

58. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መሣሪያ ተጠቃሚዎች በሽያጭ መሣሪያው የሚመዘግቡት የሽያጭ መረጃ በተሟላ መልኩ (ሁሉም) ወደ ባለሥልጣኑ የመረጃ ቋት በትክክል የማይገባ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ወደባለስልጣኑ የመረጃ ቋት የሚገባውን ብዛት ያለውን መረጃ ለማጠናቀርና ለመተንተን የሚያስችል ሲስተም ያልተዘረጋ በመሆኑ የሚገቡ መረጃዎችን በሚፈለገው መጠን መጠቀም ያለመጀመራቸው ታውቋል፡፡ እንዲሁም

ለሚመለከታቸው አካላት የይለፍ ቃል በአፋጣኝ የማያገኙ በመሆኑ መረጃዎችን ለመጠቀም እንደተቸገሩ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

59. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ባለስልጣኑ የኢትዮ ቴሌኮም ጋር በቅርበት እየሰራ መሆኑ በአሁኑ ጊዜ የቴሌ መሰረተ ልማት በመሻሻሉ በቀን ወደ 70 ሺ መረጃዎች ወደመረጃ ቋት እየመጣ መሆኑ እንዲሁም የቴል መሰረተ ልማት አስተማማኝ በሚሆንበት ጊዜ ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ መረጃዎች ሊላኩ የሚችሉ መሆኑ፣ እንዲሁም ክልሎች ከቅ/ጽ/ቤቶችና ከተማ አስተዳደሮች መሳሪያዎችን የሚቆጣጠሩበት መረጃዎች መምጣታቸውን የሚከታተሉበት ሲስተም የተዘረጋ መሆኑ፣ ነገር ግን አንዳንድ ቦታዎች የኔትዎርክ ችግር ያለባቸው ክትትል በማድረግ ሲስተሙን እንዲጠቀሙ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የይለፍ ቃልን በተመለከተ ለመረጃው ደህንነት ሲባል የሚጠይቁ አካላት ለሁሉም የማይሰጥ መሆኑ እና ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች አደረጃጀት አንድ ባለመሆኑ ምክንያት ይህን ጉዳይ ለማጣራት የመዘግየት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ብለዋል፡፡

60. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሰበሰቡትን መረጃ በሙሉ ወደ ዋናው የባለስልጣኑ ዳታ ቤዝ አለማስተላለፋቸውና በባለሥልጣን መ/ቤቱም እያስተላለፉ ለመሆናቸው አለመረጋገጡ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተሻለ የታክስ/ግብር ገቢ እንዳታገኝ እና ይህ ክፍተት ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍትና ፍትሃዊ አሰራር በማስፈን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ የሚደረገውን ጥረት እንዳይሳካ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮች መረጃ አያያዝን በተመለከተ

61. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ቅ/ጽቤቶች መክፈል የሚገባቸውን ግብር ያላሳወቁ 1506 ግብር ከፋዮች ያሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መረጃቸውን በየግብር ዘመኑ አደራጅቶ በመያዝ ያለባቸው የግብር ዕዳ እንዲከፍሉ ለማስደረግ ክትትል እና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ሥራ አቁመዋል ተብለው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፋይላቸው የተዘጉ ተብለው ከተያዙት 3362 ግብር ከፋዮች ውስጥ ሥራ እንዳቆሙ በማዕከል ደረጃ የሚታወቁት እና የተዘጉ ተብሎ በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS)

ላይ የሚታዩት 1504 ሲሆኑ ቀሪዎቹ 1858 ግብር ከፋዮች ግን በሥራ ላይ (active) እንደሆኑ የሚታይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

62. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የንግድ ስራቸውን ያቆሙ ወይም የታገዱ ግብር ከፋዮች ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ንግድ ፈቃዳቸውን ሲመልሱ ዝርዝራቸውን ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተገቢ ጥንቃቄ እንዲደረግ እና ፋይላቸው ከሲስተምና ከማህደር እንዲዘጋ መረጃ የሚሰጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

63. እንዲሁም በማዕከል የተያዙት እና በመንግስት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት ላይ ያሉ ልዩነቶች የሚከሰቱት በቅ/ጽ/ቤቶች በማህደር ከተዘጉ በውኃላ በሲስተም ላይ የተዘጋበት ቀን ሳይሞላ ከቀረ የሚፈጠር መሆኑን ገልፀው በየወቅቱ የመናበብ እና ግብረመልስ የመስጠት ችግሮች የተከሰቱ ሲሆን ችግሮቹን ለመፍታት እየሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ከላይ የተገለፁት የቁጥር ብልጫዎች በአሁኑ ወቅት ስለመስተካከላቸው ማስረጃ አላቀረቡም፡፡

64. በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙትን ግኝቶች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር የተዘጋጀ ቢሆንም አፈፃፀሙን ከግኝቶቹ ጋር በማነፃፀር መስተካከሉን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ እንዲሁም ግብር ማሳወቅና እና መክፈል ያቆሙት ግብር ከፋዮች ተለይተው አለመታወቃቸው የግብር ግዴታቸውን የማይወጡ ግብር ከፋዮች እንዲበራከቱ እና መሰብሰብ የሚገባው ገቢ በአግባቡ እንዳይሰበሰብ አስተዋጽኦ በማድረግ ፍትሃዊ አሰራር እንዳይሰፍን ያደርጋል፡፡

የመረጃ አቅርቦት መስጫ ማዕከል መኖሩን በተመለከተ

65. በክዋኔ በኦዲቱ ወቅት የመረጃ መስጫ ማዕከላት በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ያልተቋቋሙ በመሆኑ ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ማብራሪያ የማይሰጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

66. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመረጃ መስጫ ማዕከላት በዋናው መ/ቤት እና በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተቋቁሟል በተጨማሪም በዋና መ/ቤት ነፃ የጥሪ ማዕከል 8199 (call center) ተቋቁሞ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ክፍል ሶስት

የክትትል ኦዲቱ (Follow up Audit) መደምደሚያዎች

67. የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በአገሪቷ ካሉ ሰፊ የአገልግሎት ሽፋን ከሚሰጡና ገቢን ከሚሰበስቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዋናው መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ ምክንያት ዘርፈ ብዙ አገልግሎት የሚሰጥ እና አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል የሚያገለግል በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚኖሩ ችግሮች የመልካም አስተዳደር እንዳይሰፍንና ችግሮቹ እንዲጎላ የሚያደርጉ በመሆኑ አገልግሎት አሰጣጡንና አሰራሮችን በማሻሻልና በማስተካከል ግብር ከፋዩን በተቀላጠፈ ሁኔታ በማስተናገድ ግብር ከፋዩ ግብር የመክፈል ግዴታውን በፈቃደኝነትና በታማኝነት እንዲወጣ በሰፊው ትኩረት ሰጥቶ ሊያገለግል ይገባዋል፡፡ እንዲሁም በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ የተቀመጠውን መልካም አስተዳደርን ከማስፈን፣ ከማረጋገጥና ከማከናወን አንፃር የተጣለበትን ከፍተኛ ኃላፊነት እንዲወጣ ያስችለዋል፡፡

68. በመሆኑም በባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃ አስተዳደር ስርዓት ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም በሚል ከ2002-2005 በጀት አመትን የሸፈነውና በ2006 ዓ.ም ሪፖርቱ ወጪ በሆነው በክዋኔ ኦዲት ላይ የተገኙ ግኝቶች ላይ የተደረጉ ለውጦችን/መሻሻሎችን/ በክትትል ኦዲት የተዳሰሱ ሲሆን በክዋኔ ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ ከተሰጡ 20 የማሻሻያ ሃሳቦች ውስጥ 8ቱ 40% ሙሉ በሙሉ የተሻሻሉ፣ 3ቱ 15% በከፊል የተሻሻሉ እና 9ኙ 45% ያልተሻሻሉ ሲሆን በከፊልና ሙሉ በሙሉ የተሻሻሉት ግኝቶች በመልካም ጎን የሚታይና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የክዋኔ ኦዲት የሚያከናወንበትን ዓላማ እንዲያሳካ እገዛ ያደረጉ ሲሆን መሻሻል ያልተደረገባቸው ጉዳዮች አሁንም ትኩረት ተሰጧቸው መሻሻል/መቀረፍ/ ያለባቸው በመሆናቸው ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ እነርሱም ዋና ዋናዎቹ፡-

69. የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን አቅም ለማሳደግ በሚመለከተው ክፍል ተጠይቀው እስካሁን መልስ ያልተሰጣቸው የሽያጭ መረጃን የማስገቢያ ሲስተም፣ የግብር ከፋዮችን የሀብት መረጃ/ የቤት፣ መኪና እና የአክሲዮን ድርሻ/ ማስገቢያ ሲስተም ፣ የህትመት መረጃ /ለንግድ ሥራ የሚታተሙ መፅሄቶችና ጋዜጦች/፣ የመረጃ ማጠናቀሪያና መተንተኛ ሶፍትዌር /ማጠቃለያ ሪፖርት/ ሲስተም፣ ከግብር አወሳሰን ግብረ-መልስ ለማግኘት

የሚያስችል ሲስተም፣ የወጪ መጋራት መረጃ ኦን ላይን ለመሰብሰብ የሚያስችል ሲስተም፣ የ ECX መረጃን ኦን ላይን ለመሰብሰብ የሚያስችል ሲስተሞችን ያልተዘረጉ መሆኑ፤

70. የመረጃ ቋቶች እርስ በርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ (Interface & Intranet) ተደርገው ያልተሰሩ መሆናቸው እንዲሁም አቅማቸውን በማሳደግ አሁንም ችግሩ እንዲቀረፍ ያልተደረገ መሆኑ፤

71. ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ተመዝግበው የተገኙትን ግብር ከፋዮች የማጥራት ስራ ያልተሰራ መሆኑ እና በአሁኑ ወቅት ከአንድ በላይ የመለያ ቁጥር የያዘ ግብር ከፋይ የሌለ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ወይም ማስረጃ መስጠት ያልቻሉ መሆኑ፣

72. ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ሲቀይሩ በSIGTAS ያለው መረጃ ወደቀየሩበት ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ወዲያው የሚዛወር ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ማህደራቸው አብሮ የማይዛወር መሆኑ፤

73. በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (በSIGTAS) እና በቅ/ፅ/ቤቶች የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ ተመሳሳይና የሚናበብ አለመሆኑ እና ግብር ከፋዩ የሚያደረጋቸውን ማንኛውም ለውጦች በግብር ከፋይነት በተመዘገበበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እየቀረበ ማሳወቅ እንደሚገባው እና በየጊዜው የማያሳውቁ ግብር ከፋዮች ተጠያቂ የማያደርግ መሆኑ፤

74. የግብር ከፋይ መረጃዎ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ከክልሎች ጋር በደብዳቤ እና በሀርድ ኮፒ የሚደረግ ልውውጥ መሰረት መረጃዎች ወደ መረጃ ማዕከል የሚገባ ቢሆንም ወቅታዊ (up to date) አለመሆኑ እና ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው የተቀመጡ እና እየተሰበሰቡ ያሉ የሽያጭ መረጃዎች ለግብር አወሳሰን በተሟላ እና በጠራ መልኩ እንዲጠቅሙ ማድረግ አለመቻሉ ና በሚፈለገው ያክል በመረጃ የተደገፈ መደረግ አለቻሉ እንዲሁም ይህን ችግር የሚቀርፍ የመረጃ ቴክኖሎጂ አቅም ያልተገነባ መሆኑ፣

75. በ2007 በጀት ዓመት የቀረቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ከተገልጋዩ የቀረበው የቅሬታ አቤቱታ 58% የሚሆነው የህግ አግባብነት ያለውና ለባለጉዳዩ የተወሰነ በመሆኑ በቅ/ጽ/ቤቶች የቅሬታ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ፤ እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት ትንተና ሪፖርት ላይ ለበላይ

አመራሩ ቀርበው የነበሩና በአሰራር መመለስ ያለባቸው ችግሮች ላይ የአሰራር ለውጥ ያልተደረገባቸው በመሆኑ በቀጣይ አመት በድጋሚ እንደችግር የተጠቀሱ መሆኑ፤

76. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የግብር መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀት እና አስተዳደርን ወጥ እና ተመጋጋቢነት ያለው ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ ምክንያት በአገሪቱ ባሉ የግብር ማዕከላት የመረጃ አሰባሰብ ወጥነት የሌለው መሆኑ ፤

77. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አወጋገድ እና አስተዳደር ስርዓትን ለመወሰን ረቂቅ ጥናት በሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ገቢ ሰብሳቢ አመራሮች ግብዓት ተሰጥቶበት የመጨረሻ ቅርፅ የያዘ ቢሆንም መመሪያው ተግባራዊ ያልተደረበ መሆኑ፤

78. በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መሣሪያ ተጠቃሚዎች በሽያጭ መሣሪያው የሚመዘግቡት የሽያጭ መረጃ በተሟላ መልኩ (ሁሉም) ወደ ባለሥልጣኑ የመረጃ ቋት በትክክል የማይገባ መሆኑ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

ክፍል አራት

በክትትል ኦዲቱ (Follow up Audit) የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች

በ 2005/2006 ዓ.ም በኢትዮጵያ ገቢዮችና ጉምሩክ ባለስልጣን በመረጃ አያያዝና አስተዳደር አፈፃፀም ላይ ለባለስልጣኑ በቀረበ ሪፖርት የተሰጡ የማሻሻ ሃሳቦች በአብዛኛው ተግባራዊ የተደረጉ ቢሆንም የተወሰኑት ተግባራዊ ያልተደረጉ በመሆናቸው ባለስልጣን መ/ቤቱ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲተገብራቸው እንዲያደርግና በመንግስት የተያዘውን የመልካም አስተዳደርን የማበልፀግ ዕቅድ ለማሳካት የራሱን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ በድጋሚ የሚከተሉት የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን አቅም ለማሳደግ በሚመለከተው ክፍል ተጠይቀው እስካሁን መልስ ያልተሰጣቸው የሽያጭ መረጃን የማስገቢያ ሲስተም፣ የግብር ከፋዮችን የሀብት መረጃ/ የቤት፣ መኪና እና የአክሲዮን ድርሻ/ ማስገቢያ ሲስተም ፣ የህትመት መረጃ /ለንግድ ሥራ የሚታተሙ መፅሄቶችና ጋዜጦች/፣ የመረጃ ማጠናቀሪያና መተንተኛ ሶፍትዌር /ማጠቃለያ ሪፖርት/ ሲስተም፣ ከግብር አወሳሰን ግብረ-መልስ ለማግኘት የሚያስችል ሲስተም፣ የወጪ መጋራት መረጃ ኦን ላይን ለመሰብሰብ የሚያስችል ሲስተም፣ የ ECX መረጃን ኦን ላይን ለመሰብሰብ የሚያስችል ሲስተሞችን በመተግበር አገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻል ይገባዋል፡፡
- የመረጃ ቋቶች እርስ በርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ (Interface & Intranet) ተደርገው ያልተሰሩ ቢሆንም አቅማቸውን በማሳደግ ችግሩ እንዲቀረፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ተመዝግበው የተገኙትን ግብር ከፋዮች የማጥራት ስራ ሊሰራ እና በአሁኑ ወቅት ከአንድ በላይ የመለያ ቁጥር የያዘ ግብር ከፋይ እንዳይኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ሲቀይሩ በSIGTAS ያለው መረጃ እና ማህደራቸው ወደቀየሩበት ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ወዲያው በማዛወር አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (በSIGTAS) እና በቅ/ፅ/ቤቶች የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ ተመሳሳይና የሚናበብ ሊደረግ እና ግብር ከፋዩ የሚያደረጓቸውን ማንኛውም ለውጦች በግብር ከፋይነት በተመዘገበቡበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እየቀረቡ ማሳወቅ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ እና ይህን ኃላፊነት በማይወጡ ግብር ከፋዮች ተጠያቂ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የግብር ከፋይ መረጃዎ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ከክልሎች ጋር በደብዳቤ እና በሀርድ ኮፒ የሚደረግ ልውውጥ መሰረት ወደ መረጃ ማዕከል የሚገባ መረጃዎች ወቅታዊ (up to date) እንዲሆኑ ሊያደርግ እና ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው የተቀመጡ እና እየተሰበሰቡ ያሉ የሽያጭ መረጃዎች ለግብር አወሳሰን በተሟላ እና በጠራ መልኩ እንዲጠቀሙ ማድረግ እንዲሁም በሚፈለገው ያክል/መጠን/ በመረጃ የተደገፈ ለማድረግ የመረጃ ቴክኖሎጂ አቅምን ሊያሳድግ/ሊገነባ/ ይገባል፡፡
- ከተገልጋዩ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በተገቢው መንገድ በመመርመር በአፋጣኝ መልስ መስጠት እንዲሁም ቅሬታ የሚቀርብባቸውን አሰራሮች አግባብ ባለው መልኩ ደረጃ ለመፍታት ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የግብር መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና አስተዳደርን ወጥ እና ተመጋጋቢነት የሆነ አደረጃጀት በመዘርጋትና ተመሳሳይ የሆነ አሰራርን ማስፈን ይገባል፡፡
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አወጋገድ እና አስተዳደር ስርዓትን ለመወሰን ረቂቅ ጥናት ተጠናቅቆ ወደ አገልግሎት ሊገባ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መሣሪያ ተጠቃሚዎች በሽያጭ መሣሪያው የሚመዘግቡት የሽያጭ መረጃ በተሟላ መልኩ (ሁሉም) ወደ ባለሥልጣኑ የመረጃ ቋት እንዲገባ አስፈላጊውን ሁሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ይህን የክትትል ኦዲት እንድናከናውን ስለተባበራችሁን እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት ተሰጥተው የነበሩ የማሻሻያ ሀሳቦች

1. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብን ለማቀላጠፍ የዘረጋውን የመረጃ ቴክኖሎጂ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል የግብር ከፋዩን መረጃ በአግባቡ ሊያደራጅ እና ከፍተኛ ወጪ ወጥቶበት ሥራ ላይ የዋለውን የታክስ መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀትና አስተዳደር ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ለተግባራዊነቱም ስራውን ለሚያከናውኑ ባለሙያዎች አስፈላጊውን ስልጠና በመስጠት መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ መሰብሰብ ይጠበቅበታል፡፡
2. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ግብር ከፋዮች መረጃ በየደረጃው በአግባቡ መመዘገቡ፣ ሊያጣራ እና አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አለመሰጠቱን ሊቆጣጠርና ከአንድ በላይ የግብር መለያ ቁጥር የተሰጣቸውን በማጣራት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡
3. ግብር ከፋዮች ግብር ለመክፈል በተመዘገቡበት የግብር መክፈያ ጣቢያ መክፈል የሚገባቸውን ግብር መክፈላቸውን ሊያረጋግጥ፣ ሥራ አቋርጠው ከሆነም ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማቋረጣቸውን በማረጋገጥ መረጃው ወቅታዊ መድረግ ይኖርበታል፡፡
4. ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ሲቀይሩ በሰነድ ያለው መረጃ ሙሉ በሙሉ ወደ ቀየሩት የግብር መክፈያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ወይም ጣቢያ መዘዋወሩን በየጊዜው ሊያረጋግጥና በSIGTAS ያለው መረጃ ወደ ተዛወሩበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲዛወር ሊደረግ ይገባል፡፡

5. በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ በማህደር (Hard copy) የተያዙት መረጃዎች እና በ SIGTAS የተያዙ መረጃዎች ተመሳሳይ እንዲሆኑ እና እንዲናበቡ የማጥራት ሥራ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ተከናውኖ መረጃዎቹ ተመሳሳይ መሆናቸው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሊያረጋግጥ እና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግብር ከፋዮችን የግብይት (የግዢ እና የሽያጭ) መረጃዎች እና የ3ኛ ወገን መረጃዎች በተሟላ መልክ ሰብስቦ በመረጃ ቋት በመያዝ፣ በማጥራት፣ በመተንተንና የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ይጠበቅበታል፡፡

7. በባለሥልጣን መ/ቤቱ እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግብር ከፋዮች በግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ጋር በተያያዘ በየደረጃው የሚያቀርቡአቸው ቅሬታዎችና አቤቱታዎች፣ የተሰጡ ውሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃችን የሚገልጹ መረጃዎች በዝርዝር ተደራጅተው የሚያዙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

8. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ወጥ የሆነ ለታክስ ውሳኔ የሚረዳ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አሰረጫጨት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

9. በአገር አቀፍ ደረጃ ከታክስ ጋር የተያያዘ የመረጃ ልውውጥ እና የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ በፌደራል፣ በክልል መንግስታት እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል የመግባቢያ ሰነድ በሁሉም በሚመለከታቸው አካላት ተፈርሞ ሥራ ላይ እንዲውል ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

10. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮች በሙሉ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ፣ በየደረጃው ተፈጻሚ ለመሆኑ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡

11. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚጠቀምበት የቴክኖሎጂ ሥርዓት ጋር የሚጣጣምና የሚናበብ፣ ለሁሉም የሥራ ዘርፍ የሚያገለግሉ እና ተስማሚ ሆነው

ሊዘጋጁ፣ ከዚህ በፊት ሥራ ላይ የዋሉት ሶፍት ዌሮች ያለባቸው ችግር እየተፈተሸ ማሻሻያ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ዕውቅና ባልተሰጠው ሶፍትዌር የሚጠቀሙ ግብር ከፋዮች ላይ ተገቢው ክትትል እየተደረገ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

12. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ሲበላሹ በተበላሹ በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረግ እንዲሁም በስራ ላይ እያሉ በየዓመቱ እድሳት የሚደረግበት ሁኔታ ከአቅራቢዎች ጋር በመመካከር መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

13. በባለሥልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በክልሎች እና የከተማ መስተዳደሮች ግብር ከፋዮች በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚመዘገቡት የሽያጭ መረጃ ወደ ባለስልጣን መ/ቤቱ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት በትክክል መግባቱን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ፣ በየደረጃው ያሉት ግብር ሰብሳቢ አካላት ተግባራዊነቱን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚችሉበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

14. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መስፈርት አሟልተው እና ስምምነት ፈርመው በገቡት ውል መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በማያቀርቡት እና ተገቢውን የጥገና ሥራ በማያከናውኑ አቅራቢዎች ላይ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ግዴታቸውን በማይወጡ አቅራቢዎች ላይም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ይኖርበትል፡፡

15. በባለስልጣን መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መለያ ቁጥር (TIN) ተሰቷቸው ተመዝግበው እና የንግድ ፍቃድ አውጥተው የሚገባቸውን ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮች በሚመለከት በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተያዘው መረጃና በዋናው መ/ቤት የተያዘው መረጃ ተመሳሳይ እንዲሆን የማጥራት ስራ ተከናውኖ መክፈል የሚገባቸውን ግብር እንዲከፍሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

16. ባለስልጣን መ/ቤቱ የንግድ ስራቸውን ማቆማቸው ወይም መዝጋታቸው የተረጋገጠ ግብር ከፋዮች የተመዘገቡበት መለያ ቁጥር (TIN) ተመልሶ ፋይላቸው ከሲስተምም ሆነ ከማህደር እንዲዘጋ መደረጉን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

17. በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተደራጁ ለግብር አሰባሰብና አወሳሰን የሚረዱ የተለያዩ የመረጃ ቋቶች (የመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መረጃ መስብሰቢያ፣ የጉምሩክ ስነሥርዓት ለገቢ ዕቃዎም ሆነ

ለወጪ ዕቃዎች የሚከናወንበት የአሲኩዳ ሲስተም፣ የግብር ከፋይ የአሻራ ምዝገባ) ውስጥ የተያዙት መረጃዎች እርስ በእርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ (Interface) በማደረግ ለግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

18. መረጃውንም በግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ እንዲሁም ታክስ ኦዲት ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች በአግባቡ የሚጠቀሙበት መንገድ ባለሥልጣኑ ሊያመቻች ይገባል፡፡

19. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ የሚረዱ ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ በመተንትንና በማጠናቀር ጥቅም ላይ እንዲውል ለተጠቀሚዎች በተገቢው መንገድ መሰራጨታቸውን፤ እና መረጃዎችም ጥቅም ላይ መዋላቸው ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ግብረ- መልስ መሰብሰቢያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

20. ባለስልጣን መ/ቤቱ ግብር ከፋዮችም ሆኑ ሌሎች ተገልጋዮች ለሚፈልጉቸው ማብራሪያዎችም ሆነ ጥያቄዎች በቀላሉ መረጃና ምላሽ የሚያገኙባቸው ዴስኮች ወይም እንደ አስፈላጊነቱ የመረጃ መስጫ ማዕከላትን በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ በማቋቋም ለግብር ከፋዩ ወይም ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ማብራሪያ እንዲሰጥ አስፈላገውን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት ፡፡

በአጠቃላይ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግብር መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀት እና አስተዳደር ስርዓት የተጣጣመ ወጥ እና ውጤታማ እንዲሆን ሊያደርግ፣ የሚሰበሰበውም መረጃ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋሉን መከታተል የሚያስችል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ እና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እና ለክልሎች የሚያደርገውን የድጋፍና ክትትል ሂደትን በማጠናከር በአዋጅ የተሰጠውን ግዴታ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡